# መዝሙርና የሙዚቃ መሣሪያዎች

## ፩. መግቢያ

ዜማ የሥራና የምስጋና ፍጡራን ሆነው ለተፈጠሩት ሰው እና መላእክት ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጸጋ ስጦታ ነው። በዜማ ማመስገን ዋጋው እጥፍ ድርብ ከመሆኑም በላይ በንባብ ከማመስገን በበለጠ ሁኔታ መንፈሳዊ ተመስጦን የሚያመጣ በመሆኑ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ሰዎች እግዚአብሔርን በዜማ ሲያመሰግኑ ኖረዋል።

ዜማ ሲነሣ ዜማውን ለማጀብ በጥቅም ላይ የሚውሉት የዜማ መሣሪያዎች አብረው ይነሣሉ። በቤተ ክርስቲያናችን የዜማ መሣሪያዎች ጉዳይ ከተወሰኑ ዐሥርተ ዓመታት ወዲህ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኗል። በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያን የተለያየ የቴክኖሎጂ ውጠቶችን እንደምትጠቀመው ሁሉ እንደ ፒያኖና ጊታር ያሉ የዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሆኑ የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀም አለባት ብለው ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶችን የሚያቀርቡ ወገኖች ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ የዜማ መሣሪያዎች እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶች አጠቃቀም ፈጽሞ ሊነጻጸሩ እንደማይገባና እነዚህ መሣሪያዎች /የሙዚቃ መሣሪያዎቹ/ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋላቸው ሊታሰብም እንደማይገባ ያስረዳሉ። ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛውን ሐሳብ በመደገፍ የምትቀበላቸውን የዜማ መሣሪያዎች በአዋጅ ብታሳውቅም አሁንም በጉዳዩ ላይ ጥያቄ የሚያነሡ ሰዎች አልጠፉም። በዚህ ጽሑፍ የምንዳስሰውም ይህንን የቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን መምሰል አለበት የሚለውን ጉዳይ ነው።

የዜማ መሣሪያዎች የሚነሡት ከዜማ ጋር በመሆኑ በመጀመሪያ ዜማን በተመለከተ ያለውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና የተለያዩ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ተሞክሮ /ታሪክ/ እናያለን። በመቀጠል የዜማ መሣሪያዎችን ምንነትና ታሪክ እናይና ከዚህ በመነሣት ዘመናዊ የዜማ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋል አለባቸው የሚሉና መዋል የለባቸውም የሚሉ ወገኖች የሚያነሧቸውን ሐሳቦች እንዳስሳለን። በመጨረሻ በጉዳዩ ላይ ማጠቃለያ እንሰጣለን።

## ፪. ዜማ

ዜማ ማለት ስልታዊና ቀመራዊ በሆነ ሁኔታ በላህይና በቅላጼ ተዋሕዶ የሚሰማ፣ ልዩ ስሜትና ተመስጦ ሊሰጥ በሚችል መልኩ የተቀነባበረ ጨኸታዊ ድምፅ ነው።

### ፪.፩. ዜማ በመጽሐፍ ቅዱስ

ዜማ የተጀመረው በጥንተ ፍጥረት በመላእክቱ አንደበት ነው። መላእክት ከተፈጠሩ በኋላ አምላካቸውን በዜማ /በጨኸት/ አመስግነዋል። ከዋክብት በተፈጠሩ ጊዜ መላእክቱ ሁሉ በታላቅ ቃል አመስግነውታል። /ኢዮ. ፴፰፥፯/

ሰው እና መላእክት የተፈጠሩት ስሙን አመስግነው ክብሩን ለመውረስ በመሆኑ በጣዕመ ዝማሬ ማመስገንን በባሕርያቸው ውስጥ እንደ አንድ መሠረታዊ ፍላጎት አድርጐ ፈጥሯቸዋል።

የመዝሙር ዝንባሌ በእያንዳንዳችን ውስጥ ይገኛል። አንዳንዶቻችን ይህንን ዝንባሌ አውጥቶ የመግለጽ ስጦታ አለን፤ ሌሎቻችን ደግሞ የማድመጥ፣ የማጣጣምና በምንሰማው ዜማ የመመሰጥ ችሎታ አለን። /Coptic Music Selected Writings, pp. 5/

ዜማ ሰዎችን ይመስጣል። ከዚህ ከቁሳዊው ዓለም ወደማይታየው /ወደ ረቂቁ/ መንፈሳዊው ዓለም ያሸጋግራል። መንፈሳዊው ዜማ ልቡናንም ሰብስቦ ሥጋን ለነፍስ ያስገዛል። ስለዚህ የሰው ልጅ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ተብሎ የተሰጡትን ጸጋዎች ለሥጋዊ /እኩይ/ ተግባር እንዳዋላቸው ዜማንም ለሥጋዊው ዘፈን አውሎት ነው እንጂ ዜማ ከእዚአብሔር ለሰው ልጅና ለመላእክት እግዚአብሔርን ማመስገኛ ተደርጐ የተሰጠ ልዩ ስጦታ ነው። ይህም በመሆኑ ከጥንት ጀምሮ ሰዎች በዜማ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ኖረዋል። ለአዳም ዘጠነኛ ትውልድ የነበረው ኢዮቤል በገናንና መሰንቆን በማስተማሩ /የበገናና የመሰንቆ ደርዳሪዎች አባት እንደነበር/ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። /ዘፍ. ፬፥፳፩/

## ፩.፪. ዜማ በተለያዩ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት

በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ሐዋርያትና አርድእት ከዚያም በኋላ የተመሠረቱት የክርስቲያን ማኅበራት /ሐዋ. ፪/ በአብዛኛው አይሁዳውያን ስለነበሩ መጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን ጥቅም ላይ የዋለው ዜማ ጥንታዊው የአይሁዶች ዜማ ነበር። ከዚያ ክርስትና በሐዋርያት ስብከት ተስፋፋች። ቀስ በቀስም በየአካባቢው የተደራጁ መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ መዋቅሮች /መንበሮች/ ተቋቋሙ።

እነዚህ መንበሮች የሚመሩት በየሲኖዶሳቸው ነበር። እያንዳንዱ ሲኖዶስም እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ምዕመናን የሚመሩበትንና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚፈጽሙበትን ሥርዓት ያዘጋጃል። በዚህ መልኩ ከተዘጋጁት ነገሮች አንዱ የቤተ ክርስቲያን ዜማ ነው። ለንጽጽር ይረዳን ዘንድ አምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ከሚባሉት ውስጥ የግብጽ እና የሶርያ አብያተ ክርስቲያናትን ዜማ እንመለከታለን።

### ***፩.፪.፩. የግብጽ /Coptic/ ቤተ ክርስቲያን ዜማ***

ክርስትና ወደ ግብጽ ከመግባቱ ብዙ ሺህ ዓመታት በፊት በግብጽ ታላቅ የፈርዖኖች ሥልጣኔ ነበር። በዚህ ጥንታዊ የግብጽ ሥልጣኔ ውስጥ ዜማ ትልቅ ቦታ ነበረው። በዚህ ሥልጣኔ ውስጥ ሥነ ሕንጻ፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ኌጣ ኌጥና ዜማ /ሙዚቃ/ ልዩ ቦታ ነበራቸው። በየዓመቱ የሚዜሙ ልዩ ልዩ ዜማዎችም ነበሯቸው። በቤተ መንግሥትም ይህንን ዜማ ለነገሥታቱ የሚያቀርቡ ቡድኖች ነበሩ። በየቤቱ የነበሩ ሴቶችም በዜማ የተካኑ ነበሩ። /Coptic Music Selected Writings, pp. 1-2/

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ዜማ የተመሠረተው ከወንጌላዊው ከቅዱስ ማርቆስ ስብከት በኋላ ብዙም ሳይዘገይ ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የተውጣጡት ከግብጻውያን እና በእስክንድርያ በብዛት ይኖሩ ከነበሩ አይሁዳውያን ነው። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ዜማም የተዘጋጀው ሁለቱም ወገኖች አስቀድመው ይጠቀሙበት የነበረውን ዜማ ማለትም የጥንታዊውን የግብጽ ፈርዖኖች ዜማና የአይሁዳውያንን ዜማ መሠረት በማድረግ ነው። ይህ ጥንታዊ ዜማ እስከአሁን ድረስ ተጠብቆ የሚገኝ ሲሆን ጥልቅ እና ውስጣዊ ስሜትን የመግለጽ አቅም ያለው ልዩ ዜማ ነው። /Brief Notes on Coptic Hymns, pp. 22-23/

### ***፩.፪.፪. የሶርያ /Syrian/ ቤተ ክርስቲያን ዜማ***

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ዜማ የደረሰው የመንፈስ ቅዱስ የዜማ መሣሪያ እየተባለ የሚጠራው ቅዱስ ኤፍሬም ነው። ቅዱስ ኤፍሬም ልክ እንደ ቅዱስ ያሬድ የዜማ ብቻ ሳይሆን የመጻሕፍትም ሊቅ እንደሆነ አገራችን የመጡት እንደ ውዳሴ ማርያም ያሉት ድርሰቶቹ ይመሰክራሉ። የቅዱስ ኤፍሬም ዜማ በሶርያ እና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን በምዕራብ /በግሪክ እና በላቲን/ አብያተ ክርስቲያናትም ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። ይህንን የቅዱስ ኤፍሬም ዜማ ዛሬም ድረስ የሶርያ ቤተ ክርስቲያን እየተገለገለችበት ትገኛለች። /Poetry and Music of the Syriac Orthodox Chruch, pp. 1-3/

## ፩.፫. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜማ

### ***፩.፫.፩. ቅድመ ክርስትና***

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሦስቱም ሕግጋት ማለትም በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል እግዚአብሔርን ያመለከች ሀገር ናት። ዜማ ደግሞ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ለሰው ልጆች የሰጠው የማመስገኛ መንገድ በመሆኑ በእነዚህ ዘመናት በሙሉ ኢትዮጵያውያን በዜማ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ እንደነበር ግልጽ ነው። በተለይም ዘመነ አበው አልፎ ዘመነ ኦሪት ሲተካ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ታቦተ ጽዮንና ሌዋውያን አብረው ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡና የመዝሙራት መጻሕፍትም ይዘው ስለነበር ዜማው በዓይነትና በአጠቃቀም ተጨማሪ መልክ መያዙ አልቀረም። ሀገራችንም ይህንን የሌዋውያን የነበረውን አዲሱን የተደራጀ ዜማ እስከ ዘመነ ክርስትና ስትገለገልበት ቆይታለች። /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም.፣ ገጽ ፺፯/

### ***፩.፫.፪. በክርስትና ምሥረታ ወቅት***

ክርስትና ወደ ሀገራችን በ፴፬ ዓ.ም. በጃንደረባው ባኮስ አማካኝነት /ሐዋ. ፰፥፳፮/ ቢገባም ክህነት የመጣውና ምሥጢራት መፈጸም የጀመሩት እንዲሁም እምነቱ ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። በዚያን ዘመን የነበረው ዜማ እንደ አሁኑ ጥልቀት፣ ምጥቀትና ርቀት /«ቀ» ይጠብቃል/ ያለው፣ የተደራጀና የተቀነባበረ ዜማ ባይሆንም

እስራኤላውያን ባመጡት ዜማ ላይ የተመሠረተ ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ የሚሆን ዜማ ነበር። /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም.፣ ገጽ ፺፮/

### ***፪.፫.፫. የቅዱስ ያሬድ ዜማ***

አሁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበትን ዜማ የደረሰው ኢትዮጵያዊው የዜማና የትምህርት ሃይማኖት ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ በ፮ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ /፭፻፭ ዓ.ም./ በአክሱም አካባቢ ተወልዶ መጀመሪያ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በዲቁና በኋላም በዚያው በአክሱም በነበረው የትርጓሜ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሲያገለግል ቆይቷል። ከዚያም እግዚአብሔር ዝማሬ መላእክትን ሊገልጽለት ስለወደደ ሦስት ቅዱሳን መላእክትን አእዋፍ አስመስሎ በመላከ የቅዱሳን መላእክትን ዜማ አስተምሮታል። በመቀጠልም ቅዱስ ያሬድ በተመስጦ /ወደ ገነት በመነጠቅ/[1] የመላእክትን ዝማሬ በመስማት ተምሯል።

ቅዱስ ያሬድ ከዚህ በኋላ በአክሱም፣ በደብረ ዳሞ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች እየተዘዋወረ የሰማውን /የተማረውን/ ሰማያዊ ዜማ ማስተማር ጀመረ። ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፈራ። ለዚህ የቅዱስ ያሬድ አገልግሎት መሳካት በዘመኑ የነበሩት ንጉሥ አስተዋጽዖ ታላቅ ነበር። ዐፄ ገ/መስቀል የቅዱስ ያሬድን ዜማ ጣዕም ከሰሙና ከተረዱ በኋላ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መገልገያና ለሕዝቡ መባረኪያ የሰጣቸው መሆኑን ተገንዝበው ሊቃውንቱን «ተቀበሉትና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ይሁን» አሏቸው። ካህናቱ እና ሊቃውንቱ ግን «ምን ምልክት ዓይተን እንቀበለው?» በማለታቸው ሱባዔ እንዲያዝ ወሰኑ። ስለዚህ ከታኅሣሥ ፩ እስከ ፯ /በዘመኑ ከሰኞ እስከ እሑድ/ ሱባዔ ታወጀ። በየቀኑ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንን እየዞሩ እግዚኦታ እና በእንተ ማርያም ሲያደርሱ ሰንብተው በ፯ኛው ቀን ምሕላውን ጨርሰው ሲያሳርጉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ተገለጸላቸው። በዚያን ጊዜም ቅዱስ ያሬድ «ዘበመስቀሉ ተቀነው፣ ወበነቢያት ተሰብከ፣ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ሰብሕዎ፣ ኪያሁ ንሰብክ መድኅነ» ብሎ በዜማ አመሰገነ።

በዚህ ተአምር የቅዱስ ያሬድ ዜማ እውነተኛ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑ በራሱ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተመሰከረለት የቤተ ክርስቲያን መገልገያ እንዲሆን ተወሰነ። በዘመኑ የነበሩ ካህናትና ዲያቆናትም የቅዱስ ያሬድን ዜማ ተማሩ። /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም.፣ ገጽ ፻፫/

የቅዱስ ያሬድ ዜማ በሦስት ዓይነት ድምፀ ዜማ /ስልት/ የሚጮኽ /የሚዜም/ ነው። እነዚህ ሦስቱ ስልቶች ግእዝ፣ እዝል እና አራራይ በመባል ይታወቃሉ። በእነዚህ ሦስት የዜማ ስልቶች የሚዜሙ /የሚጮኹ/ በርካታ ድርሰቶችን ቅዱስ ያሬድ አዘጋጅቷቸዋል። ዋና ዋናዎቹም ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት እና ቅዳሴያት ናቸው።

የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቦታ በዜማነት ብቻ የተወሰነ አይደለም። ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ከመድረሱ በሪት የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መምህር የነበረ በመሆኑና ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢራት ስለተገለጡለት በድርሰቶቹ ውስጥ ጥልቅ የሆኑ የነገረ ሃይማኖት፣ የሥነ ምግባር እና የታሪክ ትምህርቶች ይገኛሉ። ለዚህም አንዱ ማስረጃ ትምህርቶቹ በበርካታ የአንድምታ መጻሕፍት ውስጥ መጠቀሳቸው ነው። /የቅዱስ ያሬድ ዜና ሕይወት በተለያዩ ጸሐፍት ሥራዎች ገጽ ፴፯/

## ፫. የዜማ መሣሪያዎች

የዜማ መሣሪያ ማለት ዜማ በሚዜምበት ጊዜ ዜማውን ለማጀብ፣ ድምቀት ለመስጠት ወይም የሚያዜሙት ሰዎች በአንድነት እንዲያዜሙ ለማስቻል /ኅብረታቸውንና ሪትማቸውን ለመጠበቅ/ ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ማለት ነው።

### ፫.፩. የዜማ መሣሪያዎችና መዝሙራት በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን ሰዎች እግዚአብሔርን በዜማ በሚያመሰግኑበት ጊዜ መሣሪያዎችን ይጠቀሙ እንደነበር በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመዝግቦ ይገኛል። ለምሳሌ ያህልም፡-

- «የወንድሙም ስም ኢዮቤል ነበር። እርሱም በገናንና መሰንቆ የሚደረድሩትን አስተማረ /ወሰደ/።» /ዘፍ. ፬፥፳፩/

---

[1] ቅዱስ ያሬድ የሦስቱን አእዋፍ ዝማሬ ከሰማ በኋላ አንዳንዶች በአካል ወደ ገነት ሄዶ ዜማውን ተማረ ሲሉ ሌሎች ደግሞ እዚሁ እያለ በተመስጦ ዜማ ተገለጠለት ይላሉ። /የቅዱስ ያሬድ ሕይወት በተለያዩ ጸሐፍት ሥራዎች፣ ገጽ ፲፩/

- «የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዝማሬ ከኋላዋ ወጡ።» /ዘፀ. ፲፭፥፳/
- «ዳዊትና የእስራኤልም ልጆች ሁሉ በዜማ መሣሪያዎቹ በበገናና በመሰንቆ በከበሮና በነጋሪት በጸናጽልና በእንዚራ በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይጫወቱ ነበር።» /፪ኛ ሳሙ. ፮፥፭/
- «እግዚአብሔርን በተቀደሱ ቦታዎች አመስግኑት፤ በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤ በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት፤ በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑት፤ አውታር ባለው መሣሪያ በእንዚራ አመስግኑት። ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት፤ በጸናጽልና በእልልታ አመስግኑት።» ይላል። /መዝ. ፻፶፥፩-፮/

## <u>፫.፪. የዜማ መሣሪያዎችና መዝሙራት በሐዲስ ኪዳን</u>

በሐዲስ ኪዳን የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀም እንዳለብን የሚገልጽ አንድም ምዕራፍ የለም። እንዲሁም በሐዋርያት ዘመንም ሆነ ከሐዋርያት አበው በኋላ ለብዙ መቶ ክፍለ ዘመናት ስለዜማ መሣሪያዎች የተጠቀሰ ነገር የለም። እንዲያውም ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ቅዱሳን አባቶች የዜማ መሣሪያን እንዳንጠቀም ያስተማሩበት እና ያወገዙበት ሁኔታ ነው የሚታየው። /Origin and History of Instrumental Music in Christian Worship, www.pb.org/pbdocs/music.html/

በሐዲስ ኪዳን ስለ ዜማ /መዝሙር/ የተጠቀሰባቸው ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው።

- «መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።» /ማቴ. ፳፮፥፴፣ ማር. ፲፬፥፳፮/
- «በመንፈቀ ሌሊትም ጳውሎስና ሲላስ ጸለዩ፤ እግዚአብሔርንም በዜማ አመሰገኑት።» /ሐዋ. ፲፮፥፳፭/
- «እንዲሁም አሕዛብ እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ ያመሰግኑት ዘንድ ነው። እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ «ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፤ ስለስምህም እዘምራለሁ።» /ሮሜ. ፲፭፥፱/
- «በመንፈሴ እዘምራለሁ፤ በማስተዋልም እዘምራለሁ።» /፩ኛ ቆሮ. ፲፬፥፲፭/
- «መዝሙርንና ምስጋናን የተቀደሰ ማኅሌትን አንብቡ በልባችሁም ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ዘምሩም።» /ኤፌ. ፭፥፲፱/
- «በጥበብ ሁሉ እንድትበለጽጉ የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ዘንድ ይጽና በመንፈስም ራሳችሁን አስተምሩ፤ ገሥጹ፤ መዝሙርንና ምስጋናን የቅድስና ማኅሌትንም በልባችሁ በጸጋ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።» /ቆላ. ፫፥፲፮/
- «ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤ በጉባኤም መካከል ምስጋናህን እዘምራለሁ።» /ዕብ. ፪፥፲፪/
- «ከእናንተ መካከል የሚያዝን ቢኖር ይጸልይ፤ ደስ ያለው ቢኖርም ይዘምር።» /ያዕ. ፭፥፲፫/

ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን በዜማ ማመስገንን በተመለከተ የተጻፉትን እነዚህን የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች ስንመለከት በአንድም ቦታ ላይ የዜማ መሣሪያዎች በጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚገልጽ ነገር አለመኖሩን እንረዳለን።

ይህንን አባባል ደግሞ የበለጠ የሚያጠናክረው በሐዋርያት እግር የተተኩ የተለያዩ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ዜማ መሣሪያዎች ያስተማሯቸው ትምህርቶች ናቸው።

## <u>፫.፫. የዜማ መሣሪያዎች በቀደምት አባቶች አንደበት</u>

### <u>*፫.፫.፩. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ*</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዳዊትን መዝሙራት በተረጐመበት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል «ቅዱስ ዳዊት መዝሙር ይዘምር ነበር። እኛም ዛሬ የተለያዩ ዜማዎችን እናዜማለን። እርሱ ሕይወት የሌላቸው አውታሮች ያሉት በገና ነበረው። ቤተ ክርስቲያን ግን ሕያው የሆኑ አውታሮች ያሉት በገና አላት። ምላሳችንም ሕያው የሆነ የበገና አውታር ነው። በእርግጥም ይህ የበለጠ መንፈሳዊ ነው። ስለዚህ ምንም ዓይነት መሣሪያ አያስፈልገንም፤ ይልቁንም ሥጋችንን ለነፍሳችን አስገዝተን በመዘመር መንፈሳዊ ዜማን እናውጣ።» /What did early Christians believe about using instrumental music in worship, www.bible.ca/H-music.htm/

### <u>*፫.፫.፪. ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ*</u>

«እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአምሳሉ ሲሠራው መልካም፣ ሕያው፣ ቅዱስና በዚህ ዓለም ጥበብ ከተሠሩ መሣሪያዎች የበለጠ የምስጋና መሣሪያ አድርጎ ነው። «ሳኦል በአጋንንት ተይዞ በተሰቃየ ጊዜ ቅዱስ ዳዊት በገናውን በመደርደር ይፈውሰው

ነበር። ከዳዊት ዘር የተወለደው ነገር ግን ከዳዊት በፊት የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ዓለሙን ባስተካከለ ጊዜ በገና እና ጸናጽልን አስቀርቶ የሰው ልጅ ሥጋ እና ነፍስን ተዋሕደው ልዩ ዜማ እንዲያቀርቡ ሰውም ሕያው የሆነ መሣሪያ እንዲሆን አድርጎታል።» /What did early Christians believe about using instrumental music in worship, www.bible.ca/H-music.htm/

### *፫.፫.፫. አውሳብዮስ ዘቂሳርያ*

አውሳብዮስም መዝሙር ዘጠና አንድን በተረጐመበት ድርሰቱ «በቀደመው በግዝረት ዘመን /በኦሪት/ ሰዎች በሰንበት ቀን በመሰብሰብ የተለያዩ የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀማቸው ትክክል አይደለም አያሰኝም። እኛ ግን ዝማሬያችንን በሕያው መሣሪያና በመንፈሳዊ መዝሙር እናቀርባለን ክርስቲያኖች በአንድነት ሆነው የሚያሰሙት ድምፅ /ዝማሬ/ በእግዚአብሔር ዘንድ ከምንም ዓይነት የመሣሪያ ድምፅ በላይ ተቀባይነት አለው። ስለዚህም በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ሐሳብና በስምምነት ሆነን በአንድነት በቃላችን ለእግዚአብሔር ዝማሬን እናቀርባለን።» ብሏል /What did early Christians believe about using instrumental music in worship/

በአጠቃላይ ቀደምት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች «የዜማ መሣሪያዎች በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ቦታ ቢኖራቸውም ሐዲስ ኪዳን ግን የፍጹምነት ዘመን በመሆኑ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለብን ግዑዛን በሆኑ የዜማ መሣሪያዎች ሳይሆን ሕያው በሆነው የሰው ልጅ ልሳን መሣሪያነት ጭምር መሆን አለበት» የሚል አስተምህሮ ነበራቸው።

### ፫.፬. የዜማ መሣሪያዎች በሌሎች የእምነት ድርጅቶች መሥራቾች አንደበት

ምንም እንኳን አባባላቸውና ትምህርታቸው ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምንጭ ተደርጎ ሊጠቀስ ባይችልም የሌሎች የእምነት ድርጅቶች በተለይ የፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅት መሥራቾችና መሪዎች የነበሩ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የነበራቸውን አመለካከት ማየቱም አይከፋም።

- ማርቲን ሉተር /የፕሮቴስታንት እምነት መሥራች/ «ኦርጋን የበዓል /የጣኦት ማመስገኛ/ ነው» ብሏል።
- ጆን ካልቪን /የፕሪስቢቴሪያን እምነት መሥራች/ ደግሞ «የዜማ መሣሪያዎችን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠቀም የብሉይ ኪዳን ሥርዓትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማስገባት ተለይቶ አይታይም።» ብሏል።
- አዳም ክለርክ የተባለ የመጽሐፍ ቅዱስ «ተርጓሚ» ደግሞ «እኔ ሽማግሌ ሰው ነኝ። ስለዚህ እናገራችኋለሁ በሕይወት ዘመኔ በሙሉ እነዚህ መሣሪያዎች በአምልኮ ሥርዓት ውስጥ መልካም ውጤት ሲያስገኙ አይቼ አላውቅም። ይልቁንም መጥፎ ተጽዕኖ በማሣደር የተዋጣላቸው መሆናቸውን አይቻለሁ። ሙዚቃ የማደንቀው ጥበብ ነው። ነገር ግን መሣሪያዎችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ማስገባትን አጥብቄ እቃወማለሁ።» በማለት ለሙዚቃ መሣሪያዎች ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት ገልጸዋል። /Musical instruments in the Church, www.pb.org/pbdocs/music.html/

### ፫.፭. የዜማ መሣሪያዎች በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት

የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክም የሚያሳየው የዜማ መሣሪያዎች በጥንታዊው የክርስትና ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ያልነበሩና በኋላ የተጨመሩ ነገሮች መሆናቸውን ነው። አሁንም አብዛኞቹ የኦሪየንታል እና የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ያሏቸው የዜማ መሣሪያዎች አጠቃቀም ጥቂት ወይንም ምንም ነው። ለማሳያ ይሆን ዘንድ የግብጽ፣ የሶርያ እና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ዙሪያ ያላቸውን ታሪክ /ተሞክሮ/ እና አቋም በአጭሩ እንዳስሳለን።

### *፫.፭.፩. የግብጽ ቤተ ክርስቲያን*

በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ያሉት የዜማ መሣሪያዎች ሁለት ብቻ ሲሆኑ እነርሱም Cymbals እና Triangle በመባል ይታወቃሉ። ሁለቱም መሣሪያዎች ብረትን በብረት በመምታት ድምፅ የሚያወጡ ናቸው።

በCoptic Studies Institute የሙዚቃ ዲፓርትመንት አባል ከሆኑት ከዶ/ር ራግሔብ ሞፍታህ ጋር የተደረገን ቃለ መጠይቅ መሠረት አድርጎ የተጻፈ አንድ ጽሑፍ እንዲህ ይላል።

«በኢየሩሳሌም በነበረው የአይሁድ ቤተ መቅደስ የሙዚቃ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚገኙ ምኩራቦች ግን የሙዚቃ መሣሪያዎችን አይጠቀሙም። ሐዋርያት ለክርስትና የመረጡት የምኩራብ ሥርዓትን ነው።

ይህም ምርጫ የሰውን ድምፅ ብቻ ለዜማ መጠቀም ነው። ይህም በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ዳግም ተረጋግጧል። በዕለተ ሰንበት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ነገሥታት በውኃ ኦርጋን ታጅበው ይመጡና ከቤተ ክርስቲያኑ ኦርጋኑን ሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ በመተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይገቡ ነበር። ይህም የድምፅ ምስጋናን የማክበር ምልክት ነው። መሣሪያ አልባ ምስጋና በብዙ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እስከ አሁን ድረስ ተጠብቆ ይገኛል። በእኔ እምነት ጉሮሮ እጅግ በጣም ጥሩው የዜማ መሣሪያ ነው። እንዲሁም ሕያው እና ከነፍስ እና ከስሜት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የማመስገኛ መሣሪያ ነው።

«አሁን በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የምንጠቀምባቸው Cymbals እና Triangle በኋላ ዘመን የመጡና ተገቢ ያልሆኑ ጭማሪዎች ናቸው። ጥቅማቸውም ሁሉም ምዕመናን በአንድነት ሲዘምሩ ሪትሙን ጠብቀው እኩል መዘመር እንዲችሉ ለመርዳት እንጂ በኮፕት ዜማ ላይ ምንም ዓይነት አስደሳች ነገር /melody/ አይጨምሩም። ነገር ግን ይህንን ጥንታዊ ትውፊት ለማስወገድ መሞከር ማንም ሰው ሊያስበው የማይገባ መጥፎ አድጋ ነው።» /Copts and Coptic Hymns, Shenouda Mamdouh, pp. 2/

### ፫.፭.፪. የሶርያ ቤተ ክርስቲያን

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ኤፍሬም አማካይነት የተዘጋጀውን ጥንታዊ ዜማን የምትጠቀም ሲሆን እስከ ፲፱፻፴ ድረስ በአገለግሎቷ የሙዚቃ መሣሪያን ያልተጠቀመች ቢሆንም በዚህ ዘመን በፓትርያርክ ኤልያስ ፫ኛ ዘመን ኦርጋንን መጠቀም ጀምራለች። በሶርያ ቤተ ክርስቲያን እምነት ምንም እንኳን የሙዚቃ መሣሪያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት መጠቀም መንፈስን የሚያነሣሣ እንደሆነ ቢታመንም ከመጠን ያለፈ ሲሆን ግን መንፈሳዊ አገልግሎትን ሊረብሽ ይችላል ብለው ያምናሉ። በተለይ ምዕመናንን በዜማ እንዳይሳተፉ በሚያደርግበት ወቅት ይህ ጐልቶ ይታያል ብለው ይላሉ። /Syrian Church Music, www.sor.cua.edu/Syriac_Orthodox_Music.html/

### ፫.፭.፫. የግሪክ ቤተ ክርስቲያን

በአሜሪካ የሚገኝ የአንድ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ድረ ገጽ እንደሚገልጸው በአሜሪካ ያሉት የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት ለጋብቻ ሥርዓት /ለምሥጢረ ጋብቻ/ ብቻ ኦርጋን የሚባለውን የሙዚቃ መሣሪያ ይጠቀማሉ። ይህም የተደረገው ኦርጋን የአሜሪካ የሠርግ ትውፊት አካል ስለሆነ ነው። ከዚህ ውጪ ምንም ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ አይጠቀሙም። /http://www.stconstantinehelen.org/spiritual_guidance.html/

### ፫.፭.፬. የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ጥበብ /The Catholic Encyclopedia/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ የሚከተሉትን መረጃዎች ይዟል።

- ለብዙ መቶ ዓመታት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ አትጠቀምም ነበር።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ኦርጋን የተባለው የዜማ መሣሪያ በጥቅም ላይ የዋለው በፓፓ ቪታሊየን /Pope Vitalion/ ጊዜ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን /በ፮፻፷፫ ዓ.ም./ ነው።
- ይህ ነገር ቀስ በቀስ እያደገ መጥቶ በዐሥራ ስድስተኛውና በዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የዜማ መሣሪያዎች በስፋት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጥቅም ላይ መዋል ጀመሩ።
- እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች በአገልግሎቷ ላይ አሉታዊ ነገሮችን መፍጠራቸው ያሳሰባት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ይህን በተመለከተ የተለያዩ ዐዋጆች /ቀኖናዎችን/ በተለያዩ ጊዜዎች አውጥታለች /ደንግጋለች/። ለምሳሌ ያህል:-
    - ቤኔዲክት ፲ኛ በ፲፯፻፵፱ ከኦርጋን ውጪ ሌሎች መሣሪያዎችን ምሥጢራት በሚፈጽሙበት ጊዜ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ደንግጓል።
    - በጎርጎርዮስ ፲፮ኛ ስም የሮሙ ካርዲናል ቪክተር በ፲፰፻፶፮ ያወጣው ዐዋጅ ደግሞ እንዲህ ይነበባል። «ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ሊቀርብ የሚገባው ዝማሬ በሰው ድምፅ /vocal/ ብቻ ቢሆንም በኦርጋን የታጀበ ዜማ ማቅረብም ይፈቀዳል። በዚህ ጊዜ የዘማሪዎች /የምዕመናን/ ድምፅ ጐልቶ መሰማት አለበት። የመሣሪያው ድምፅም ሊውጠው አይገባም።

ከዚህ በተጨማሪ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት ያላት ዝንባሌና ጥረት የዜማ መሣሪያዎችን ትቶ በድምፅ ብቻ ወደ ማመስገን መመለስ መሆኑን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ጥበብ ይገልጻል።

## ፫.፮. የዜማ መሣሪያዎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

### ፫.፮.፩. ቅድመ ያሬድ

ሕገ ኦሪትና ታቦተ ጽዮን ወደ ሀገራችን ሲመጡ ሌዋውያኑ መጻሕፍቶቻቸውንና ዜማቸውን እንዳመጡት ሁሉ የዜማ መሣሪያዎቻቸውንም ይዘው መጥተዋል። ለዚህም ማስረጃው ዛሬ በሀገራችን ያሉት አብዛኛዎቹ የዜማ መሣሪያዎች በእስራኤል ዘንድ የነበሩና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ወይም ከእነዚያ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ ከበሮ፣ በገና፣ መሰንቆ፣ ጸናጽል፣ ወዘተ … በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ይገለገሉባቸው ከነበሩት መሣሪያዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት አላቸው።

ክርስትና ወደ ሀገራችን ከገባ በኋላም እስከ ቅዱስ ያሬድ መነሣት ድረስ በነበረው ዘመን ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ዜማ ይኸው በመሆኑ መሣሪያዎቹም ጥቅም ላይ ውለው ሊሆን ይችላል።

### ፫.፮.፪. በቅዱስ ያሬድ ዘመን

ቅዱስ ያሬድ የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀምን በተመለከተ ያለው አቋም አስቀድመን እንዳየናቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች /እንደነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ፣ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ …/ በመሆኑም ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ አልተጠቀመም። ነገር ግን አንዳንዶች መቋሚያና ጸናጽል የቅዱስ ያሬድ የዜማ መሣሪያዎች እንደሆኑ ሲናገሩና በቅዱስ ያሬድ ሥዕል ላይም ተቀምጠው እናያለን። ይሁን እንጂ ጉዳዩ የበለጠ ጥናት ተደርጐ እስካልተረጋገጠ ድረስ ተጠቅሟል ለማለት አያስደፍርም።

የቅዱስ ያሬድ የራሱ የሆኑት /original/ ድርሰቶች ዛሬም ድረስ ያለ ዜማ መሣሪያዎች የሚዜሙ ናቸው። እነዚህም ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት እና ቅዳሴ ናቸው።

ዳግማዊ ያሬድ የሚባሉትና በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት እንደ ቅዱስ ያሬድ የመጻሕፍትና የዜማ ሊቅ የነበሩት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ያደረጉት እንደ ቅዱሳን አባቶች እና እንደ ቅዱስ ያሬድ ነው። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በቅዱሳን መጻሕፍት እና በቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች የተካኑና ራሳቸውም ሰዓታትን የመሰለ ድንቅ የዜማ ድርሰት የደረሱ ቢሆንም ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያዎችን አልተጠቀሙም።

ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን /ጥምቀት፣ ቁርባን፣ ተክሊል …/ በሚፈጸሙባቸው አገልግሎቶች ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ አትጠቀምም። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያናችን በዐቢይ ጾም ወቅት በአንዳንድ ገዳማት ሁልጊዜ የዜማ መሣሪያዎችን አንጠቀምም።

### ፫.፮.፫. ድኅረ ቅዱስ ያሬድ /ማኅሌት /አቋቋም/ ከ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ/

አስቀድመን እንደገለጽነው ቅዱስ ያሬድ የደረሰው ዜማ ያለምንም የዜማ መሣሪያ የሚዜም /የሚጮኽ/ ነበር። ይህም ዜማ /በተለይ በድጓው ያለው/ ቁም ዜማ ይባላል። አሁን የምንጠቀምበትና ከቁም ዜማው ምልክትና ላህይ ሳይወጣ የሚባለውና ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችና ከሌሎች ሊቃውንት ድርሰቶች ጋር በማቀነባበር ከከበሮ፣ ከመቋሚያና ከጸናጽል ጋር ተስማምቶ በረጅሙ የሚዜም ዜማ ማኅሌት ወይም አቋቋም ይባላል።

ማኅሌትና አቋቋም የቅዱስ ያሬድን ዜማ እና ድርሰት /ዘር/ እንዲሁም የሌሎች ሊቃውንትን ድርሰት /ዘር/ በመጠቀም የተዘጋጁት በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ በጎንደር በነበሩ ሊቃውንት እንደሆነ ይነገራል። /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም.፣ ገጽ ፳፩/

አሁን በቤተ ክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት /በቤተ መቅደስ ውስጥ/ የምንጠቀምባቸውም የዜማ መሣሪያዎች ማለትም ከበሮ እና ጸናጽል እንዲሁም መቋሚያ በጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ከአቋቋም /ማኅሌት/ መዘጋጀት በፊት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ቁም ዜማ ብቻ ስለሆነ ይህ ቁም ዜማ ደግሞ ምንም ዓይነት መሣሪያ ስለማይጠቀም ነው።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ማስተዋል ያስፈልጋል። የዜማ መሣሪያዎች ብለን በጥቅል የተመለከትናቸውን ነገሮች በሁለት ክፍሎ መመልከት ይገባል።

፩. ተያያዥ /continuous/ የሆነ ዜማ የሚያወጡ የዜማ መሣሪያዎች /እንደ መሰንቆ፣ በገና፣ ዋሽንት … የመሳሰሉት/

፪. ብቻቸውን ምንም ዓይነት ዜማ /ተያያዥ /continuous/ የሆነ ድምፅ/ የማያወጡና የዜማ ምትን /ሪትምን/ ብቻ ለመጠበቅ የሚረዱ የዜማ መሣሪያዎች ለምሳሌ እንደ ከበሮ፣ ጸናጽል እና መቋሚያ ለዚህ ምሳሌ ናቸው።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለው አገልግሎት ጥቅም እየሰጡ ያሉት በሁለተኛው ክፍል የሚመደቡ ሲሆን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ባሉት መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ያሉት ደግሞ በመጀመሪያው ይመደባሉ።

በማኅሌት ዜማ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ሰዎች በጉሮሯቸው የሚያወጡት ድምፅ ነው። የከበሮው፣ የጸናጽሉና የመቋሚያው አገልግሎት በብዛትና በኅብረት ሆነው የሚያገለግሉት ካህናት ወይም መዘምራን ድምፃቸውን እኩል ማውጣትና ማዜም እንዲሁም ማጨብጨብ እንዲችሉ /ወይም ሪትማቸውን እንዲጠብቁ/ ማስቻል ነው። ከዚህ ውጭ ከበሮው፣ ጸናጽል እና መቋሚያው ብቻቸውን ሊያወጡት የሚችሉት ትርጉም ያለው ዜማ የለም። በማኅሌት ጊዜም የሰዎችን ድምፅ የሚተኩ ሆነው ሳይሆን የዘማሪዎችን የድምፅ አጣጣል ለማስተባበር ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያናችንን የዜማ መሣሪያዎች አጠቃቀም ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያስረዳል። ምክንያቱም በግብጽ ቤተ ክርስቲያን አሁን ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት መሣሪያዎች /Cymbals እና Triangle/ ያላቸው ሚና አሁን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ከበሮና ጸናጽል ያላቸውን ዓይነት ስለሆነ።

ሌላው የዜማ መሣሪያ መቋሚያ ሲሆን እሱም ሁለት ጥቅሞች አሉት። ለዝማሜ እና ለምርኩዝነት ወይም ለድጋፍ ያገለግላል። እንደ ዜማ መሣሪያ የሚያገለግለው ለዝማሜ ሲውል ብቻ ነው። ይህም ከመሬት ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ድምፅ ስለሚያወጣ ሲሆን ሁኔታውም ከላይ ከተጠቀሰው ከጸናጽልና ከበሮ ጋር ተመሳሳይ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን ምሥጢራትን ለመፈጸም ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ ባትጠቀምም፣ እንዲሁም ለውስጥ አገልግሎት /ማኅሌት/ የምትጠቀምባቸውም የዜማ መሣሪያዎችም ከላይ ያየናቸው ጸናጽል፣ ከበሮ እና መቋሚያ ብቻ ቢሆኑም በአፍአ /ከቤተ መቅደስ ውጭ ላሉ አገልግሎቶች/ ለሕዝቡ የምትፈቅዳቸው የዜማ መሣሪያዎችም አሉ።

እነዚህም መሣሪያዎች መሰንቆ፣ በገና፣ ዋሽንት፣ እምቢልታ እና መለከት ሲሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት መሣሪያዎች /ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ/ ጋር በቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ መመሪያ አንቀጽ 26 ከቁጥር 1-4 ተደንግገዋል።

## ፫.፮.፩. የዜማ መሣሪያዎችና ሁለቱ ኪዳናት

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሦስቱም ሕግጋት /ሕገ ልቡና፣ ሕገ ኦሪት እና ሕገ ወንጌል/ እግዚአብሔርን ያመለከች ሀገር ነች። ክርስትናን ከመቀበላችን በፊት በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን እያመለክን የኖርን መሆናችን ከሌላው ዓለም በሙሉ ልዩ ያደርገናል። በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ በቤተ ክርስቲያን ያሉ የአምልኮ ሥርዓቶች እና ክርስቲያናዊ ባሕሎች የብሉይ ኪዳንን እና የሐዲስ ኪዳንን ምሥጢር አስተባብረው የያዙ ናቸው። እነዚህ ሥርዓቶችም የሚሰጡት መንፈሳዊ ትርጉም በእውነት ልዩ ነው። ለምሳሌ ታቦት ወይም ጽላት በብሉይ ኪዳን ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እግዚአብሔር በረድኤት እየተገለጠ ሕዝቡን የሚያነጋግርበት የአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ ነው። ሀገራችንም በሕገ ኦሪት ሳለች በዚሁ መልኩ ስትጠቀምበት ኖራለች። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ይህ ቅዱስ ንዋይ ልዩና ለሐዲስ ኪዳን የሚስማማ ድርብ ትርጉም እና አገልግሎት ተሰጥቶት እየተጠቀምንበት እንገኛለን። በዘመነ ረድኤት እግዚአብሔር በረድኤት ይገለጥበት የነበረው ንዋይ ቅዱስ ዛሬ በዘመነ ጸጋ እግዚአብሔር በጸጋው ከእኛ ጋር አንድ የሚሆንበት ቅዱስ ሥጋው እና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት ሆኗል። በፊት እግዚአብሔር ለሰው ፈጽሚቸው እንዲድንባቸው የተሰጡት ዐሥርቱ ቃላት ኦሪት ይጻፍበት የነበረው ዛሬ ለሰው ልጆች ፍጹም ድኅነት እንዲሆን ተብሎ የተሰጠው የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ስምም የሚጻፍበት ሆኗል።

ቅዳሴ ሊቀደስ ካህኑ በዘመነ ረድኤት /በብሉይ ኪዳን/ እግዚአብሔር በረድኤት ይገለጥበት በነበረው በታቦት /ጽላት/ ላይ አድርገው ዛሬ በዘመነ ጸጋ /ሐዲስ/ እግዚአብሔር በጸጋ ከሰው ልጆች ጋር አንድ የሚሆንበትን የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት የክርስቶስን አማናዊ ሥጋና ደም ሲሰጡበት ማየት በእውነት በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለውን የጥላነት እና የአካልነት ግንኙነት የሚያሳይ አስደናቂ ክብር ያለው ምሥጢር ነው።

ቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎችን በተመለከተ ያደረገችውም ይህንኑ ነው። ሐዲስ ኪዳን የፍጹምነት ዘመን በመሆኑ ያለምንም መሣሪያ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት ዘመን ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት በሚፈጸሙባቸው አገልግሎቶች ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ አትጠቀምም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለየት ብላ ብሉይ እና ሐዲስን አስተባብራ የያዘች በመሆኗ ክርስትና ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል ለኦሪት አምልኮ ስንጠቀምባቸው የኖሩትን እና በሃይማኖታዊ ትውፊታችን ትልቅ ቦታ ያላቸውን የዜማ መሣሪያዎች /በገና፣ ዋሽንት፣ እምቢልታ፣ መለከት እና መሰንቆ/ ለአፍአዊ አገልግሎት እንዲውሉ አድርጋለች።

ከነዚህም መካከል ተከታታይ የሆነ /continuous/ ዜማ /melody/ የሚያወጡት ከበሮ፣ ጸናጽል እና መቋሚያ ተመርጠው ምሥጢራት ለማይፈጸምበት የውስጥ የማኅሌት አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል። የሌሊቱ አገልግሎት በእነዚህ ሲፈጸም ያድርና ጠዋት ምንም መሣሪያ በማይጠቀመው ጸሎተ ቅዳሴ ይጠቃለላል። የአፍአው አገልግሎት ደግሞ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ ስንጠቀምባቸውና በቤተ ክርስቲያንም በአዋጅ የወሰንናቸውን መሣሪያዎች በመጠቀም ይካሔዳል።

## ፬. ወደፊትስ?

### ፬.፩. መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ስትጠቀም ኖራለች። አሁንም የተለያዩ ዓይነት የድምፅ ማጉያዎች /sound systems/ ለቅዳሴና በስብከት አገልግሎት እንጠቀማለን። የኤሌክትሪክ መብራት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ኢንተርኔትንም ለትምህርተ ወንጌል ማስፋፊያ እየተጠቀምንበት እንገኛለን። ሌላም ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን።

«የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን እንደ ፒያኖ፣ ኦርጋን፣ ጊታር፣ ሳክስፎን፣ አኮርዲዮን የመሳሰሉትን የዜማ መሣሪያዎችንም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠቀም አለብን» የሚል ሐሳብ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ቤተ ክርስቲያን ይህንን በማድረጓ ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞች እንዳሉም ይናገራሉ።

በዚህ የጽሑፋችን ክፍል መጀመሪያ እነዚህ ሰዎች ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይገኛሉ የሚሏቸውን ጥቅሞች ካቀረብን በኋላ በመቀጠል ይህንን ማድረጉ ያሉትን ጉዳቶችና አሉታዊ ተጽዕኖዎች እንመለከታለን። ከዚህ በፊት ግን አንድ ነገር ለማንሣት እንወዳለን። ይህም የሙዚቃ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እንዲውሉ ሊወሰን የሚችለው እንዴት ነው? የሚለውን ነው። የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች ምንጭ የሆኑና ቤተ ክርስቲያን የምትመራባቸው ሦስት ነገሮች አሉ። እነሱም ዶግማ፣ ቀኖና እና ትውፊት ናቸው። እነሱም ከዚህ በታች በከፊል ይብራራሉ።

***ዶግማ፡-*** *መሠረተ እምነት /ሃይማኖት/ ሲሆን ትምህርተ ሃይማኖት ተብለው የሚገለጹና በነገረ እግዚአብሔር /አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት/ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እና በነገረ ቅዱሳን ዙሪያ ቤተ ክርስቲያን ያላትን አስተምህሮ የሚገልጹ ናቸው። ዶግማ የማይቀየር እና የማይሻሻል ቋሚ የሆነ እግዚአብሔር በቅዱሳን መጻሕፍትና በቅዱሳን አባቶች አማካኝነት የገለጠው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ነው።*

**ቀኖና፡-** ቃለ ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ መጠን፣ ልክ ማለት ሲሆን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚፈጸምበት፣ ሥርዓት የሚደነገግበት፣ የመጻሕፍት ቁጥር፣ የቅዱሳን ቁጥር፣ የበዓላት ቁጥርና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት ወዘተ ... የሚወሰንበት ማለት ነው።

**ትውፊት፡-** ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ጀምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ ቁሳውያን፣ ቃላውያን፣ ሥዕላውያን የሆኑ መልካም መንፈሳዊ ባሕሎችን የሚያካትቱ የቃል ውርሶች ናቸው። በዚህ ውስጥ የአነጋገር፣ የአበላል፣ የቅርስ፣ የአለባበስ ወዘተ ... ባሕሎቻችን ይካተታሉ።

ቀኖና እና ትውፊት ግን እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜውንና ቦታውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሻሻሉ የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ በእምነት አንድ የሆኑ አምስቱ /ስድስቱ/ የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት አንድነታቸው በዶግማ ነው እንጂ በቀኖናና በትውፊት የየራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ይለያያሉ።

ዜማ እና የዜማ መሣሪያዎች ክፍላቸው ከቀኖናና ከትውፊት ነው። በመሆኑም ተገቢ ሆኖ ከተገኘ በእነዚህ ዙሪያ ያለው የቤተ ክርስቲያን አቋም ጊዜንና ሁኔታን ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ሊስተካከል ይችላል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ቀኖና

እንዲቀየር የምትፈቅደው እንዴት ነው? ምንስ ሒደቶች መታለፍ አለባቸው? ቀኖናዉን መቀየር የሚችለውስ ማን ነው? የሚሉትን ነጥቦች በትክክል መረዳት ያስፈልጋል።

በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ሊቀየር የሚችሉባቸው ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ። /በዓላት፣ ገጽ ፪፻፫/ እነዚህም፦

- በዘመኑ የሚነሱ ውዝግቦችን ለመፍታትና ሰዎችን ለጽድቅ በሚያበቃቸው መንገድ ለመምራት። ለምሳሌ በ፶ ዓ.ም. የተደረገው ጉባኤ ከአሕዛብ ወገን ወደ ክርስትና የተመለሱትን ሰዎች በአይሁድ መንገድ ለመምራት ቢሞከር ጭርሱኑ ክርስትናውን ሊተዉት እንደሚችሉ በመገንዘብ ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሥርዓት ተሠርቶላቸዋል። /ሐዋ. ፲፭፥፩-፴፩/
- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶችን /አገልግሎቶችን/ ባለው ነባራዊ ሁኔታ መፈጸም እንዲችሉ ለማድረግ። ለምሳሌ በመጀመሪያዎቹ መቶ ክፍለ ዘመናት ጥምቀት የሚከናወነው ወደ ወንዝ ተወርዶ ወንዙ በሐዋርያት /በካህናት/ ከተባረከ በኋላ ተጠማቂዎችን ወደ ወንዙ ውስጥ በመጥለቅ /በመዝፈቅ/ ነበር። በአሁን ዘመን ግን ይህን ለመፈጸም ሁኔታዎች ስለማያስችሉ ጸሎት /ሥርዓተ ቅዳሴ/ የደረሰበትን ውኃ በተጠማቂዎች ላይ በማፍሰስ እንዲፈጸም ሥርዓት ተሠርቷል።

ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ሊያሟላ የሚችል ነገር ሲፈጠር ቀኖናው የሚሻሻል ሲሆን ቀኖናን ሊቀይር የሚችለው የቤተ ክርስቲያን አካል ደግሞ ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ነው። ይህም በሚደረግበት ጊዜ ጉዳዩን ማጥናትና የጥናቱንም ውጤት በጥሞና መመርመርና መገምገም ውሳኔውን ሊቀድም ይገባዋል። ይህ ከሆነ ጥልና ክርክርን አስወግዶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጸጥታ ወደብ የሚያደርስ ውሳኔ መወሰን ይቻላል።

## ፬.፪. የሙዚቃ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለዜማ አገልግሎት መዋል አለባቸው የሚሉ ወገኖች የሚያነሧቸው ሐሳቦች

### ፬.፪.፩. ብዙዎችን /በተለይ ወጣቶችን/ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት ስለሚረዳ

በዘመናችን ያሉት ፈጣኖቹና ለሰው ሁሉ በጣም ቅርብ የሆኑት ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በአብዛኛው የሚያቀርቡት በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ ዜማዎችን በመሆኑ እነዚህ መሣሪያዎች በጣም ተለምደዋል። በብዙዎችም ዘንድ ተወዳጅ ናቸው። ይህም ብዙዎች /በተለይ ወጣቶች/ የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በሚያዘጋጇቸው በዘመኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚዘጋጁ መዝሙሮች በመሳብ ወደ እምነታቸው እንዲገቡ ከማድረጉም በላይ ያልገቡትም መዝሙሮቻቸውን በፍቅር እንዲያዳምጡ እያደረገ ይገኛል። እነሱም ይህንን እንደ ጥሩ አጋጣሚ እየተጠቀሙበት ነው። ስለዚህ የኛም ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ዓይነት መዝሙሮችን በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ብታዘጋጅ ወደ ሌላ እምነት ያልገቡትን ከመጠበቁም ባሻገር የገቡት ሊመለሱ ይችላሉ።

### ፬.፪.፪. ሰዎች በችሎታቸው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ስለሚያደርግ

የሙዚቃ መሣሪያዎችን የመጫወት ችሎታ ያላቸው ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን የሙዚቃ መሣሪያዎችን ብትፈቅድ እነዚህ ሁሉ ሰዎች በችሎታቸው እግዚአብሔርን የማገልገል ዕድል ያገኛሉ።

## ፬.፫. የሙዚቃ መሣሪያዎችን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ መጠቀም ያሉት ጉዳቶችና አሉታዊ ተጽዕኖዎች

### ፬.፫.፩. ዜማን ዓላማውን ያስቱታል

በመግቢያው እንደተናገርነው በዜማ እግዚአብሔርን የማመስገን ዋናው አስፈላጊነት ዜማ ከንባብ የበለጠ ተመስጦን ስለሚያመጣና ሥጋን ለነፍስ አስገዝቶ ወደ ሰማያዊው ዓለም የሚያሸጋግር ኃይል ስላለው ነው።

### ፬.፫.፪. ሐዲስ ኪዳን የፍጹምነት ዘመን ነው

ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት መጠቀም በዜማ ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽዕኖ አስመልክተን ያነጋገርናቸው የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ምሩቅና የሥነ ሙዚቃ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሠርፀ ፍሬ ስብሐት «የምዕራባውያን ዜማ እና የዜማ መሣሪያዎች ዛሬ ያሉበትን ቅርጽ ያገኙት ሦስት ደረጃዎችን አልፈው ነው።» ይላሉ። የመጀመሪያው ደረጃ «ፍጹምነት» /absolutism/ ሲሆን ዜማ እና የዜማ መሣሪያዎች ሙሉ በሙሉ ለመንፈሳዊና ለአምልኮ አገልግሎት የዋሉበት ዘመን ነው። ከዚህ ዘመን ከነበሩት መሣሪያዎች መካከል church organ፣ violin፣ እና piano

ይጠቀሳሉ። ሁለተኛው ደረጃ «ዓለማዊነት» /secularism/ ነው። ይህ ዘመን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይውሉ የነበሩ ዜማዎችና መሣሪያዎች ዓለማዊ ሐሳቦችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉበት ዘመን ነው። ሦስተኛውና አሁን ያለንበት ደረጃ «ስሜት» /emotion/ ነው። ይህ ዜማዎችና የዜማ መሣሪያዎች ስሜትን እንዲገልጹ እየተደረገበት ያለ ዘመን ነው። ለምሳሌ ስለጦርነት ለተዘፈነ አንድ ዘፈን የሚዘጋጅ ዜማ የጦርነት ስሜትን እንዲፈጥር ተደርጎ ይቀነባበራል። ስለ ፍቅር፣ ሐዘን፣ ዝሙት ወዘተ ... የሚዘጋጁ ዜማዎችም እንደዚሁ እያንዳንዱ በዘፈኑ የሚንጸባረቀውን ስሜት እንዲፈጥሩ ተደርገው ይቀነባበራሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን መሣሪያዎችም የሚሠሩት እነዚህን ስሜቶች መግለጽ የሚችሉ ድምፆችን እንዲያወጡ ተደርገው ነው።

«ስለዚህም» ይላሉ አቶ ሠርፀ «አሁን ያሉትን ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሚዘጋጁ ዜማዎች በአብዛኛው ሰዎችን ወደ መንፈሳዊ ተመስጦ መውሰድ ስለማይችሉና እንደውም የዓለማዊነትና የኃጢአት ስሜቶችን የመፍጠር አዝማሚያቸው ከፍተኛ ስለሆነ መሣሪያዎቹን በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ መጠቀም አደገኛ ነው።»

በብሉይ ኪዳን የነበረው መንፈሳዊነት ፍጹም አልነበረም። ሕጉን ለሚፈጽሙ የሚሰጠው ሽልማት በአብዛኛው ነፍስን ሳይሆን ሥጋን በዋናነት የሚጠቅም ወይም አፍአዊ ነበር። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

- እናትና አባትህን አክብር፣ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥር ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም /ዘፀ. ፳፥፲፪/ የሚለውን ሕግ ስንመለከት ሕጉን ለሚፈጽሙ ሰዎች የሚሰጠው ሽልማት ሥጋዊ ድኅነት ወይም በዚህ ምድር ላይ ብዙ መኖር መሆኑን እናያለን።
- የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች /ዘሌ. ፩-፯/ የሚያስገኙት ድኅነት የሥጋ ወይም አፍአዊ ብቻ ነበር። ነፍስን ፍጹም በሆነ መልኩ ለመፈወስ የሚችሉ አልነበሩም።

በዚሁ አንጻር በብሉይ ኪዳን የነበረው የዜማ መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲሁ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ሥጋዊነት የተቀላቀለበትም እንደነበር የመሣሪያዎችን አጠቃቀም የመዘገቡ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያሳያሉ።

«ከዚያም የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮዋን ያዘች... ማርያምም ፈረሱን ፈረሰኛውን በባሕር ውስጥ ጥሏል ለእግዚአብሔር ዘምሩ፣ እጅግም ከፍ ከፍ ብሏልና እያለች ዘመረችላቸው።» /ዘፀ. ፲፭፥፳/

«ዳዊት ፍልስጤማውያንን ከገደለ በኋላ ሰዎቹ ወደቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ ሴቶች ከበሮና መሰንቆ ይዘው እየጨፈሩና እልል እያሉ ንጉሥ ሳኦልን ለመቀበል ወጡ።» /፩ኛ ሳሙ. ፲፰፥፮/

«የእግዚአብሔር ታቦት በሰረገላቸው ላይ ሆኖ ይሔድ ነበር። ዳዊትና የእስራኤል ቤት በሙሉ በዝማሬ፣ በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ በጸናጽል ... በእግዚአብሔር ፊት ያሸበሽቡ ነበር።» /፪ኛ ሳሙ. ፮፥፫-፭/

«በግብዣዎቻቸው ላይ በገናና መሰንቆ ከበሮና ዋሽንት እንዲሁም የወይን ጠጅ አለ።» /ኢሳ. ፭፥፲፩-፲፪/

ይሁን እንጂ ሐዲስ ኪዳን የፍጹምነት ዘመን ነው። በመሣሪያ የታጀበ ምስጋና ሳይሆን ነፍስና ሥጋ በአንድነት ተዋሕደው ከልብ የሆነ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ዘመን ነው። ይህንን የሚያስረዳንም፦

- በሐዲስ ኪዳን የዜማ መሣሪያን ስለመጠቀም ምንም ያለመጠቀሱ፤
- በሐዋርያት ዘመን ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያ ጥቅም ላይ አለመዋሉ፤
- እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ያሉ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ እንደ አውሳብዮስ ያሉ የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ አሳምረው የሚያውቁ የታሪክ አባቶች የዜማ መሣሪያዎች በፍጹም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል እንደሌለባቸው ማስተማራቸው፤
- በብዙ አብያተ ክርስቲያናት /ግብጽ፣ ሶርያ፣ ካቶሊክ፣ ግሪክ .../ የዜማ መሣሪያዎችን በቤተ ክርስቲያን የዜማ አገልግሎት ላይ መጠቀም ጥንት የነበረ ሳይሆን በኋላ የተጨመረ ነገር መሆኑና እሱም ጉዳት እያደረሰ መሆኑ፤
- የመላእክትን ዝማሬ ተምሮ የቤተ ክርስቲያናችንን ዜማ የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያዎችን አለመጠቀሙ ነው።

እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ደስ መሰኘትና መመስጥ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ምናልባት አብዛኞቻችን ተመስጦን ደርሰንበት አጣጥመነው ስለማናውቅ የቅዱሳን አባቶችን አባባል ሙሉ በሙሉ መረዳት ሊከብደን ይችላል። በግርድፉ ግን መመሰጥ ማለት የዚህን ዓለም ሐሳብ ትቶ ፍጹም መንፈሳዊ ወደ ሆነ ሐሳብ መግባት፣ እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ በሐሳብ ወደ ሰማያት መሔድና እንደ መላእክት የሚያስብበት ደረጃ ላይ መድረስ ማለት ነው።

አባቶቻችን በመሣሪያ የተቀነባበረ /የታጀበ/ ዘፈን «አያስደስትም» አላሉም። «አይመስጥም፣ የሰዎችን ልብ ለእግዚአብሔር አስገዝቶ በተመስጦ እንደ መላእክት መንፈሳዊ ሐሳብ እንዲያስቡ አያደርግም፤ ብሎም መንፈሳዊነትን አስረስቶ ወደ ሥጋዊ ስሜትና ደስታ ይወስዳል» አሉ እንጂ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓትም በዐቢይ ጾም ወቅት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማኅሌት አገልግሎት የምንጠቀማቸው የዜማ መሣሪያዎች እንኳን ጥቅም ላይ አይውሉም። ይህም መከበር እና መታሰብ ያለበት ወቅት በመሆኑ ነው።

ስለዚህ በአጠቃላይ የዜማ መሣሪያዎች በአግባቡ ካልተያዙ ዜማን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠበት ዓላማ እንዲያፈነግጥ የማድረግ ከፍተኛ አቅም ስላላቸውና ሐዲስ ኪዳን ደግሞ በፍጹምነት የምናገለግልበት ዘመን በመሆኑ አሁን ያሉንን የዜማ መሣሪያዎች እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንዳለብን ልናስብ ልንመካከር ይገባናል እንጂ ሌሎቹን ለኪሳራ የዳረጉትን ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብተን ለተጨማሪ ፈተና መንገድ መክፈት የለብንም።

### ፩.፫.፫. ያሬዳዊነት

የዜማ መሣሪያዎች ግን ለቤተ ክርስቲያን ያሬዳዊ ዜማ ትልቅ አደጋ መሆናቸውን ባለሙያዎች ያስረዳሉ። የሥነ ሙዚቃ ባለሙያው አቶ ሠርፀ የምዕራባዊያኑም /ዘመናዊም/ ሆነ የሀገራችን የዜማ /የሙዚቃ/ መሣሪያዎች ያሬዳዊ ዜማን ለማጀብ በሁለት ምክንያቶች አቅም እንደሌላቸው ያስረዳሉ።

የመጀመሪያው ምክንያት የምዕራባውያን የዜማ መሣሪያዎች በበቀሉበት የዓለም ክፍልና በሀገራችን ያለው የዜማ ባሕልና ስልት የተለያየ መሆኑና የእነርሱን መሣሪያዎች ከእኛ ዜማ ጋር ማዋሐድ አስቸጋሪ መሆኑ ነው። አቶ ሠርፀ «በጣም ረቂቅ ከሆነው ከያሬዳዊ ዜማ ጋር ቀርቶ ከዘመናዊው የሀገራችን ሙዚቃ ጋር እንኳን ሙሉ በሙሉ ሊዋሐዱ አይችሉም።» ይላሉ።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የምዕራባውያን ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሣሪያዎች የሚገኙት ሰባት ድምፆች ባሉበት የዲያቶኒክ ቅኝት /diatonic scales/ ውስጥ፣ የሀገራችን ባሕላዊ ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሣሪያዎች ደግሞ የሚገኙት አምስት ድምፆች ባሉበት የፔንታቶኒክ ቅኝት /pentatonic scales/ ውስጥ ሲሆን የቅዱስ ያሬድ ዜማ ግን ከሁለቱም የሚተርፍ በርካታ ድምፆች ያሉት መሆኑ ነው። «ስለዚህም» ይላሉ አቶ ሠርፀ «አምስት ወይም ሰባት ድምፅ ባላቸው የሀገራችንም ሆነ የምዕራባውያን /ዘመናዊ/ የሙዚቃ መሣሪያዎች ያሬዳዊ ዜማ ሊቀነባበር /ሊታጀብ/ አይችልም። ይህም ያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት በነበርንበት ወቅት በተደጋጋሚ ሞክረን ያረጋገጥነው ነው።»

በታሪክ ነገሥት በአታ ለማርያም መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና የካህናት ማሠልጠኛ የቅዳሴ መምህር የሆኑት መጋቤ ኅሩያን የማነ ብርሃንም በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ። «አንድ ያሬዳዊ ዜማ የሚዘጋጀው ያሬዳዊ ቅርጽ ያላቸውንና የፊደል ቅርጽ የሌላቸውን ምልክቶች /ጭረት፣ ርክርክ፣ ቅናት፣ ድፋት፣ ወዘተ .../ በመጠቀም ነው። እነዚህን የዜማ መሣሪያዎች በመጠቀም እንደ ርክርክና ጭረት ያሉትን ለማውጣት አቅም ስለሚያንሳቸው ለመዝለል ይገደዳሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ያሬዳዊ ዜማን ማጀብ አይችሉም ማለት ነው።» ይላሉ።

ከእነዚህ ነጥቦች በመነሣት አሁን ያሉት የአማርኛ መዝሙሮቻችን አብዛኞቹ ያሬዳዊ ባልሆነ ዜማ እንዲዜሙ ካበቋቸው ምክንያቶች አንዱ የዜማ መሣሪያዎች አቅም ማነስና አጠቃቀም መሆኑን መረዳት እንችላለን። በመጀመሪያ እነዚህን የዜማ መሣሪያዎች በመጠቀም ያሬዳዊ ዜማን ማዘጋጀት አይቻልም። ያሬዳዊ የሆነ ዜማ ቢደረስ እንኳን በእነዚህ መሣሪያዎች ለማጀብ በሚሞከርበት ጊዜ መሣሪያዎች ያሬዳዊውን ዜማ ማጀብ ስለማይችሉ ዜማውን መሣሪያዎች ማጀብ ወደሚችሉት ቅኝት መለወጥ እና መቀየር ግድ ይሆናል። በዚህ መልኩ ቀስ በቀስ በመሣሪያዎቹ በመነተት የመዝሙሮቻችን ዜማዎች ያሬዳዊ ባልሆኑት በእነዚህ ቅኝቶች /ትዝታ፣ አንቺሆዬ፣ ባቲ፣ አምባሰል እና ብርቱካኔ/ ለመዘጋጀት በቅተዋል።

### ፩.፫.፬. የቤተ ክርስቲያን የቀደመ ተሞክሮ

ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት ምሥጢራት በሚፈጸሙበት የአገልግሎት ጊዜ ምንም ዓይነት የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀም ባይፈቅድም በአንድ ወቅት /በ፲፱፻፷ዎቹ/ እነዚህ መሣሪያዎች ቅኔ ማኅሌቱን አልፈው ወደ ቅድስቱ ገብተው በቅዳሴ ወቅት ምስባክ አገልግሎት ማጀቢያ ሆነው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ በዚያው ወቅት በብዙ ሰንበት ት/ቤቶች የተለያዩ ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በአገልግሎት ላይ ውለው ነበር። በዚያን ጊዜ የነበራቸው ተጽዕኖ በበርካታ ሀገረ ስብከቶች በሥራ አስኪያጅነት ላገለገሉትና በአሁን ወቅት በመንበረ

ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የዕቅድና ልማት መምሪያ ምክትል ኃላፊ ከሆኑት በወቅቱ ደግሞ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የወጣቶች ጉዳይ ክፍል ኃላፊ ሆነው ሲያገለግሉ ከነበሩት ከሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገን ነበር።

ኦርጋን የሚባለው የሙዚቃ መሣሪያ እንዴት ለአገልግሎት ሊውል ቻለ? ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ «እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ መዋል የጀመሩት በ፲፱፻፷ዎቹ መጨረሻ አካባቢ «ኢየሱሳውያን» ብለው ራሳቸውን የሰየሙትን የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅት አባላት ወጣቶችን በመንጠቅ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የፈጠሩትን ችግር ለማስቆም በተቋቋመው የሰንበት ት/ቤት አባላት አማካይነት ነበር። በዚያን ጊዜ «ኢየሱሳውያኑ» እነዚህን መሣሪያዎች ለአገልግሎታቸው ይጠቀሙ ስለነበር የዚያን አጸፋ ለመመለስ ተብሎ ነው የተጀመረው። ቀስ በቀስም ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት የምስባክ ማጀቢያ እስከመሆን ደረሰ።» ብለውን ነበር።

እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ምን ዓይነት ውጤት አስገኙ? ብለን ላነሣነው ጥያቄ ደግሞ «ምንም። ኦርጋኑ በምስባክ ጊዜ ጥቅም ላይ በዋለበት ጊዜ ምስባኩ ምልክቱን ጠብቆ በትክክል ሲዜም ፒያኖው ማጀብ ስለማይችል ዜማው ያለምልክቱ ይለጠጥ ነበር። አንዳንዴም ዜማው በየመሐሉ እንዲቆረጥ ይደረግ ነበር። ከዚያም ባሻገር እንደተፈራው ሰውን ዘፋኝ አደረጉት። ወደ አንድ የዘፈን ትርኢት /ኮንሰርት/ ስትሔዱ እና ወደ አንድ የሰንበት ት/ቤት አዳራሽ ስትሔዱ የምታዩት ነገር ተመሳሳይ ነበር። ሥርዓታችን እና መንፈሳዊ እሴታችን ወደ ተራ እና መንፈሳዊ ወዳልሆነ ሥርዓትና ግብር ተለውጦ ነበር» የሚል መልስ ነበር የሰጡን።

በመጨረሻም መሣሪያዎቹ እንዴት ከቤተ ክርስቲያን ሊወጡ እንደቻሉ ሲያብራሩ «በመሠረቱ በቤተ ክርስቲያን ትውፊትና ሥርዓት መሠረት እንኳን ከቀኖናው ውጭ ያሉ መሣሪያዎችን በአገልግሎት ላይ ማዋል ቀርቶ ድምፀ መልካም የሆነ አገልጋይ እንኳን ድምፁን ለቆ እንዲጮኽ አይፈቀድም። ድምፁ /ዜማው/ ወደ ሥጋዊ ሐሳብ እንዳይወስድና ምሥጢሩን እንዳይሸፍን ድምፁን መለስ ቀለስ አድርጎ መጮኽ አለበት። ዜማው ሥጋዊ ድምቀት እንዳይኖረው እስከዚህ ድረስ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ስለዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች አዝማሚያቸው መጥፎ እና ለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት አደጋ መሆናቸው ስለታወቀ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን በቶሎ ቀጨችው።» ብለው ነበር።

## ፮. ማጠቃለያ

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ በአንድ ወቅት የተናገሩት ነገር ነበር። በግብጽ የነበሩ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ዶግማ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እና የሕይወት ትምህርት አታስተምርም የሚል ነቀፋ በተደጋጋሚ ሲሰነዝሩብን እኛም የተከላከልን እና እነሱን ያቀረብን መስሎን የዶግማውን ትምህርት ትተን የሕይወት ትምህርት ብቻ ማስተማር ጀመርን። ይሁን እንጂ እነሱን መመለስ አልቻልንም፣ የዶግማው ትምህርትም እንደተረሳ ቀረ። እነሱን ልናመጣቸው ወጥተን ለእራሳችን ወጥተን ቀረን። የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑት የዜማ መሣሪያዎች ይኖሩታል ተብለው ከቀረቡት ጥቅሞች አንዱ ሰዎችን በለመዱትና በሚወዱት ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ማቅረብ ያስችላል የሚል ነው። በእርግጥም እነዚህን መሣሪያዎች የሚጠቀሙ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች በተለይ የወጣቱን ቀልብ መሳብ ችለዋል።

ነገር ግን የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ያጋጠማት ነገር በእኛም እንዳይደርስ አርቆ ማሰብና ማስተዋል ይገባል። እነዚህን የዜማ መሣሪያዎች የተጠቀሙ የእምነት ድርጅቶች ምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማጥናትና ከዚያም መማር ያስፈልጋል። በአውሮፓ እና በአሜሪካ ያሉ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች በእነዚህ መሣሪያዎችና ሌሎችም ዘመን አፈራሽና የሕዝቡን ቀልብ የሚስቡ ነገሮች በመጠቀም ብዙ ሰዎችን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመሳብ የራሳቸው ማድረግ ችለው ነበር። ነገር ግን እነዚህን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጠቀማቸው መዝሙራቸውን ቅጥ አሳጥቶ እንደ ራፕ ባሉ የሙዚቃ ስልቶች ሳይቀር የሚዜም አድርጎታል። በአንድ ቡና ቤትና በአንድ «የአምልኮ ስፍራ» የሚሰማው ድምፅ አንድ ዓይነት እንደሆነ የዓይን ምስክር የሆኑ ሰዎች ይናገራሉ። የዚህም ውጤት አሳዛኝ ሆኗል። የፕሮቴስታንት እንዲሁም የካቶሊክ «የአምልኮ ስፍራ" የነበሩ ብዙ ቤቶች ዛሬ ወደ ሆቴልነት፣ ጭፈራ ቤትነትና ንግድ ድርጅትነት ተቀይረዋል።

በሀገራችንም ያለው ሁኔታ ወደዚያው እያመራ መሆኑን ብዙ ነገሮች ይጠቁማሉ። በ፲፱፻፹ዎቹ ይወጡ የነበሩ የፕሮቴስታንት መዝሙሮችና ዛሬ ያሉትን መዝሙራት የሚያወዳድር ሰው በሃያ ዓመታት ውስጥ ብቻ ምን ያህል እንደተለወጡ ሊያስተውል ይችላል። በዚህም ምክንያት ብዙ የፕሮቴስታንት መዝሙራት ለጫት መቃሚያነት የሚመረጡ ሆነዋል። የፕሮቴስታንት መዝሙራት እዚህ ደረጃ ለመድረሳቸው የመሣሪያዎቹ አጠቃቀም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ብዙዎች እነዚህን የዜማ መሣሪያዎች በአግባቡና በጥንቃቄ ልንጠቀምባቸውና ሊያስከትሉት የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ ልናስቀር እንችላለን ብለው ያስባሉ። አባቶች የሚናገሩት አንድ ተረት አለ። በአንድ ወቅት የዱር አራዊት በሙሉ ለጦርነት ይወጣሉ። በጦርነቱ ይሸነፉና ብዙዎች ይሞታሉ። የተረፉት ሲመለሱ ከኤሊ ጋር በመንገድ ይገናኛሉ። አራዊቱ ወዴት እንደምትሔድ ኤሊን ሲጠይቋት «ወደ ጦርነቱ» ብላ መለሰች። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎችን መጠቀም ያደረሰባትን ጉዳት ዓይታ የዜማ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የተለያዩ አዋጆች ማውጣቷን ከዚህም አልፋ እንደ ጥንቱ ያለዜማ መሣሪያዎች ወደ ማገልገል ለመመለስ ጥረት እያደረገች መሆኗን ተመልክተናል። የፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅቶች ደግሞ ለዚህም ሳይበቁ የደረሰባቸውን አይተናል። በሀገራችን ያሉትም የነገሩን አዝማሚያ በማየት የእኛን ጸናጽልና ከበሮ ማንሣትና የኅብረት መዝሙራትን መጠቀም እየጀመሩ ነው።

ይህን ሁሉ ወቅታዊ መረጃ እየሰማን የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም መሞከር ቤተ ክርስቲያናችንን በምሳሌው ላይ እንዳየናት ብዙዎች ተሸንፈው ወደጠፉበትና የተረፉትም እጅ ሰጥተው እየተመለሱበት ወዳለ ጦርነት እየሔደች እንዳለችው ኤሊ መሆን ይሆንብናል።

ጌታችን በወንጌል ካስተማረን ድንቅ ሕጎች አንዱ አርቆ ማጠርን ነው። «... ወደ ሴት ያየ የተመኛትም አመነዘረ» የሚለው ሕግ የተሰጠው አንድም አርቆ ለማጠር መሆኑን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያብራራሉ። በዚህም ጉዳይ ላይ ቤተ ክርስቲያን መከተል ያለባት አቋም ይኸው ነው። «ሳይደርቅ በእርጥቡ፤ ሳይርቅ በቅርቡ...» እንዲሉ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

*ምንጭ፡- ሐመር ልዩ እትም ነሐሴ ፳፻፩ ዓ.ም.፣ ገጽ ፵፪-፶፱*